OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የ2025 ዓ.ም Cultural Facilities Fund (የባህል ተቋማት ፈንድ) መመሪያ

## የገንዘብ ድጎማው አጠቃላይ እይታ

Cultural Facilities Fund በሲያትል የሚገኙ የሥነ-ጥበብ፣ የባህል እና የቅርስ ድርጅቶችን በተቋማዊ ፕሮጀክቶቻቸው ይደግፋል። ዓላማችን ፍትሐዊ ባልሆነ መንገድ የንብረት ባለቤት ከመሆን፣ ንብረት ከማስተዳደር ወይም ከመከራየት ለተገለሉ ሰዎች የተሻለ ተደራሽነት ማቅረብ ነው።

**ማመልከቻ፣ ብቁነት ወይም ኦንላይን የቴክኒክ ድጋፍ ዙሪያ መረጃ እና ድጋፍ ለማግኘት** የCultural Facilities Fund ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጁን በCulturalFacilitiesFund@seattle.gov ወይም ያነጋግሩ ወይም የኢጋር፣ የትምህርት እና የገንዘብ ድጎማ ሥራ አስኪያጅ የሆኑትን Ashraf Hashamን (አሽራፍ ሃሻም) በ206-514-1057 ደውለው ያነጋግሩ።።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪድዮ በኩል) ጨምሮ እርስዎ በሚፈልጉት ቋንቋ ሊያነጋግሩዎ የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** እርስዎ ብቻ ደውለው የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። ጥሪውን የሚቀላቀል አስተርጓሚ እስከምናገኝ ድረስ ለአፍታ ይጠብቃሉ።

## ማመልከቻ

በኦንላይን ያመልክቱ፦ https://seattle.fluxx.io/user_sessions/new

ለCultural Facilities Fund እና Centering Art & Racial Equity (ሥነ-ጥበብ እና የዘር እኩልነትን ያማከሉ) ፕሮግራማችን በአንድ ላይ ለማመልከት ፍላጎት ላላቸው ድርጅቶች እነዚህ ሁለት የገንዘብ ድጎማዎች ተመሳሳይ የኦንላይን ማመልከቻ የሚጠቀሙ ይሆናል።

የኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት ተደራሽነት ከሌለዎት ያሳውቁን እና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ አማራጮችን ለማግኘት ከእርስዎ ጋር አብረን እንሠራለን።

## የሚያበቃበት ቀን

**ማክሰኞ፣ ኦገስት 5 ቀን 2025 ዓ.ም 5 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር**

እባክዎ ማመልከቻዎን ሞልተው ለማጠናቀቅ በቂ ጊዜ እንዲኖርዎ ያድርጉ። ከማብቂያው ቀኑ 5 ፒ.ኤም (ፓሲፊክ) በኋላ ገቢ የሚደረጉ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

## ብቁነት

- መቀመጫውን በሲያትል ያደረገ እና በይፋ የተመዘገበ የሥነ-ጥበብ፣ የባህል፣ የቅርስ ወይም የሥነ-ጥበብ አገልግሎት ድርጅት መሆን አለብዎት።
    - ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት ሆነው በይፋ የተመዘገቡ ወይም ለትርፍ ባልተቋቋመ ድርጅት በገንዘብ የሚደገፉ መሆን አለብዎት።
    - ለትርፍ የተቋቋመ ድርጅት ሆነው በይፋ የተመዘገቡ መሆን የሚችሉ ቢሆንም፣ በቅርብ ጊዜ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት ያገኙት አጠቃላይ ዓመታዊ ገቢ ግን ከ$5,000,000 መብለጥ የለበትም።
- በተቋማዊ ዘረኝነት እና ጭቆና ከፍተኛ ተጽዕኖ ያደረባቸውን ማኅበረሰቦች የሚወክሉ መሆን እና/ወይም ሁሉን አቀፍ በሆነ መነጽር ፀረ-ዘረኝነት የሆነ ድርጅት ለመሆን ቁርጠኝነት ማሳየት አለብዎት።
- ቢያንስ ለሶስት ዓመታት ለሲያትል ነዋሪዎች ሕዝባዊ ጥቅም ያስገኙበት ታሪክ ሊኖርዎት ይገባል።
- ሲያትል ውስጥ በሂደት ላይ ያሉ ሥነ-ጥበባዊ ወይም ባህላዊ ስኬቶች ማስገኘትዎን ማሳየት መቻል አለብዎት።

- የፌደራል ግብር ከፋይ መታወቂያ ቁጥር መያዝ፣ የሲያትል ከተማ አስተዳደር የንግድ ፈቃድ መያዝ እና መቀመጫዎን በሲያትል ከተማ ማድረግ አለብዎት።

የሥራ ቦታ አጠቃቀም እና ቁጥጥር መብት፡-

- እንደ የአዋጭነት ጥናቶች፣ ሥነ-ህንፃ ወይም የምህንድስና አገልግሎቶች ላሉ "ቅድመ-ግንባታ" ወጪዎች የሥራ ቦታ አጠቃቀም እና ቁጥጥር መብት አስፈላጊ አይደለም።
- ለተቋም ማሻሻያ፣ ለህንፃ እድሳት እና ለሌሎች በግልጽ ግንባታ የሆኑ ፕሮጀክቶች ተቋሙን በባለቤትነት ወይም በኪራይ መያዝ አለብዎት (ቢያንስ ለአምስት ዓመታት የሚዘልቅ የሥራ ቦታ አጠቃቀም እና ቁጥጥር መብት መያዝ፤ ይህም የኪራይ ውልዎ ላይ የቀሩትን ዓመታት እና የባለቤቱን ፈቃድ ሳያገኙ በግልዎ የኪራይ ጊዜውን ለማራዘም ያለዎትን አማራጭ ያጠቃለለ ሊሆን ይችላል)።

## የገንዘብ ድጋፍ

ቀጥተኛ የፕሮጀክት ወጪዎችን ለመደገፍ **ከ$50,000 የማይበልጥ** ገንዘብ መጠየቅ ይችላሉ። የሚሰጠው ገንዘብ ከተጠየቀው በታች ሊሆን ይችላል። **ከሁለት የገንዘብ ድጋፍ ደረጃዎች መካከል ለአንዱ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ።**

ከ$25,000 የማይበልጡ ማመልከቻዎች በደረጃ አንድ ይታያሉ። ከ$25,000 ጀምሮ እስከ $50,000 የሚሆኑ ማመልከቻዎች በደረጃ ሁለት ይታያሉ። የደረጃ ሁለት አመልካቾች ለCultural Facilities Fund ከማመልከታቸው በፊት የፕሮጀክት በጀታቸው 50 በመቶ የተረጋገጠ መሆኑን ማሳየት መቻል ይኖርባቸዋል።

## የመረጃ ወርክሾፖች

በዚህ የገንዘብ ድጎማ እና እንዴት ምርጥ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ በሚለው ዙሪያ ተጨማሪ ለማወቅ ምናባዊ ወርክሾፕ ይቀላቀሉ። በእያንዳንዱ ወርክሾፕ የመጀመሪያው አንድ ሰዓት ለCentering Art & Racial Equity የገንዘብ ድጎማዎችን ማመልከት ላይ ያተኩራል። ይህንን የCultural Facilities Fund የገንዘብ ድጎማ አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ የማወቅ ፍላጎት ካለዎት ሙሉውን 90 ደቂቃ ለመታደም ማቀድ ይኖርብዎታል።

**ወርክሾፕ 1**
ሐሙስ፣ ሜይ 29 ቀን 2025 ዓ.ም ከ10:30 ኤ.ኤም - 12:00 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
እባክዎ 5/29 ላይ እንደሚታደሙ ያሳውቁ

**ወርክሾፕ 2 የአሜሪካ የምልክት ቋንቋ (ASL)፡- አስተርጓሚ ይኖራል**
ሰኞ፣ ጁን 2 ቀን 2025 ዓ.ም ከ2:30 – 4:00 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
እባክዎ 6/2 ላይ እንደሚታደሙ ያሳውቁ

**ወርክሾፕ 3**
ማክሰኞ፣ ጁን 24 ቀን 2025 ዓ.ም ከ12:00 ፒ.ኤም - 1:30 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
እባክዎ 6/24 ላይ እንደሚታደሙ ያሳውቁ

**ወርክሾፕ 4**
ረቡዕ፣ ጁላይ 9 ቀን 2025 ዓ.ም ከ1:00 - 2:30 ፒ.ኤም በፓሲፊክ ሰዓት አቆጣጠር
እባክዎ 7/9 ላይ እንደሚታደሙ ያሳውቁ